# ክብረ ድንግል ።



ድንግል ማርያም ሆይ ለምኚልን ።

ከሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፭ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ. ም

www.ethiopianorthodox.org

# ክብረ ድንግል ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በነገሡ በ፴፫ኛው
ዘመን መንግሥት በ፲፱፻፶፭ ዓ. ም.

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በሆኑ በ፬ተኛው
ዓመት ይህ መጽሐፍ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ከሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፭ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

ይኽ መጽሐፍ በቅድስት ማርያም ስም ብዙ ቤተ ክርስቲያን ላሣነፁት ልዩ ልዩ በጐ አድራጐት ፈጽመው በክብር ለአረፉት ለግርማዊት እቴጌ መነን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ተሰጠ "የጻድቅ መታሰቢያው ለዘለዓለም ይኖራል" (መዝ ፻፲፪ ፩ ) ።

# ክ ብ ረ ድ ን ግ ል ።



ድንግል ማርያም ሆይ ለምኚልን ።

www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም ።

ቅድስት ማርያም ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ ሁና በፍጥረቱ ሁሉ ክብር ይገባታል ፣ ይኽንም አብነት ከቅዱሳን አበው ነሥተናል ።

መልአኩ ቅ/ገብርኤል ከገለጠበት ዕለት ጀምሮ በሰዎች ዘንድ ያለማቋረጥ ትመሰገናለች ። ራሷ ቅ/ማርያም ከዛሬ ጀምሮ ፍጥረቱ ሁሉ ያመሰግኑኛል ስትል እግዚአብሔር ከደረገላት ቸርነት ፩ኛው ምስጋና እንዲገባት ማድረጉ እንደ ሆነ ራሷ ገልጣ ተናገረች ። እንግዲህ ይኽን ሰምቶ ይኽንንም ተመልክቶ እርሷን የማያመሰግን ከፍጥረት ተራ የወጣ እንደሆነ ቅ/መጽሐፍ ያስረዳናል (ሉቃ/፩ ፣ ፵፰) ።

የጥንት አባቶች ይኽን ቅዱስ ቃል በመከተል እመቤታችን ድንግል ማርያምን መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን እያሉ ድርሰት ደርሰው ዝማሬ ጽፈው አመስግነዋታል ። ጥንታውያን የሆኑት አብያተ ክርስቲያናት በዚሁ መሠረት ከጥንት ጀምረው እስከሁን እመቤታችንን ሲያመሰግኑ ፣ አማላጅነቷንም ሲያምኑና ሲገልጡ ይገኛሉ ። ከጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ፩ኛዋ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች ምእመናኗ ስለ ቅድስት ማርያም ትድግና ሲናገሩ፣ተአምራቷን ሲመሰክሩ፣ በቃል ኪዳኗም ሲጸኑ፣ በአማላጅነቷ ሲያምኑ ፣ እርሷንም ሲያመሰግኑ ይገኛሉ ። ስለ ቅድስት ማርያም ምስጋና ፣ ዝማሬ ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የተጻፉ መጻሕፍት የተደረሱ ድርሰናት ብዙ ናቸው ፣ በዚህም መሠረት አባቶች እናቶች ሁሉ በየዕለቱ አማልጅን ለምኝልን ፣ ሳይሏት አያድሩም አይው

www.ethiopianorthodox.org

## መቅድም ፡፡

ሉም ፤ ግን ብዙው የጸሎትና የምስጋናው መጽሐፍ በግዕዝ ቋንቋ ስለ ተጻፈ የአሁኑ ዘመን ወጣትም ብዙ ጊዜ ወደ ውጭ ቋንቋ እንጅ ወደእኛው ቋንቋ ወደ ግዕዙ ብዙ ዝንባሌ ስለሌለው ስለ ቅድስት ማርያም ብቻ ሳይሆን ስለማንኛውም በግዕዝ የተጻፈውን ሁሉ ለማስታወስ ችግር ሳይገጥመው አልቀረም ፡፡

ይኸም ሊሆን የቻለው ስለ ማናቸውም ነገር በተለይም ስለ ቅድስት ማርያም ምስጋና የተጻፉት በግዕዝ ስለሆን ነው ፡፡

ስለቅድስት ማርያም ክብርና ምስጋና አማላጅነትም በአሁኑ ዘመን የባዕድ አስተያየት በዝቶ ስለሚነገር የጊዜው ሕዝብ ስለ ድንግል ማርያም ያለው ፍቅር በርዶ ከእውነተኛው ሥርዓት ተወግዶ ይገኛል ፤ ስለዚህ ስለቅድስት ማርያም ከተደረሱት ከልዩ ልዩ መጻሕፍት የተወጣጣውን በ፲፱፻፷ ዓ. ም. በራዲዮ ለምእመናን በየለቱ ያሰማሁትን አሁን "ክብረ ድንግል" በሚል አርስት የሰየምኩትን ለሁሉም ደገኛውን መንገድ ለመግለጥ ጻፍኩ ፡፡

አንዳንድ ጥንታውያን ክርስቲያን አገሮች አገራችንን ለድንግል ማርያም አሥራት ተሰጥታለች እያሉ ከአባቶች ተያይዞ የመጣውን ደገኛውን ሥርዓት ሲያወሩ ይገኛሉ፤ በዚህም ዓይነት ኢትዮጵያ የድንግል ማርያም ዓሥራት እንደሆነች ጥንታውያን አባቶች ያስረዳሉ ፤ ጥንታውያን መጻሕፍትም ይመሰክራሉ ፡፡ ሁሉን መርምሩ ፤ የተሻለውንም ያዙ ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው (፩ኛ ተሰሎ|፭·፲፱) ስለቅድስት

## መቅድም ፡፡

ማርያም ያሉትን የነበሩትን ፤ የሐዋርያትን ፤ የመላእክትን ፤ የአባቶችን ፤ አስተያየት ተመልክተን በዕርግጥ ምስጋና የሚገባት መሆኗን ተረድተን እንድናመሰግናት በአማላጅነቷም ጸንተን እንድንኖር ዕውነትን የተመረኰዘውን አስተያየቴን ለሁሉ አብራራለሁ ፡፡

በሀገራችን የቅድስት ማርያም ፍቅር ከመጽናቱ የተነሣ በየጠቅላይ ግዛቱ በሚገኘው ቤተ ክርስቲያን በበለጠ ተሰይሞ የሚገኘው በቅድስት ማርያም ስም ነው ፤ ጸሎቱና ምስጋናውም በብዛት ስለቅድስት ማርያም ይደረጋል ፡፡ ብዙ የክርስትና ስሞችም በቅድስት ማርያም ስም ይጠራሉ ፡፡ ማኀበርም በዝቶ የሚከፈለው በማርያም ስም ነው ፤ በጠቅላላው ስለድንግል ማርያም ያለው የሕዝባችን አስተያየት እስካሁን ከፍ ያለ ነው፤ ቅድስት ማርያምም ለሕዝባችን ለሀገራችን አማላጅነቷንና ቃል ኪዳኗን ያለማቋረጥ ስታደርግልን በመኖሯ ይኸው ነፃነታችን ሥርዓታችን ተጠብቆ ለመኖር ቻለ ፡፡ አሁንም በርሷ አማላጅነት ተጠብቀን ለመኖር እንችል ዘንድ ለእርሷ የሚገባውን ምስጋና ልመና ልናቀርብ ይገባናል ፡፡ ምስጋናም ከማቅረባችን በፊት ስለ እርሷ ደህና አድርጎ ማወቅ አስፈላጊ ስለሆነ ይኸን በመጠኑ እገልጣለሁ ፡፡

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ልአኩን የቅ| ገብርኤልን ብሥራትና ምስጋና የቅድስት ኤልሳቤጥን እማኄና ምስጋና ከተቀበለች በኋላ «እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል» (ሉቃ| ፩፥፵፰) ስትል ተናግራለች ።

ይህን ሁሉ ምስክር ከተቀበሉ በዚህም ሁሉ ምስክር ከተረዱ በኋላ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ድርሰት በመጻፍ ፥ ምሥጢሩን አጕልቶ ፤ ምሳሌውን በመተርጐም ቅድስት ማርያምን አመስግነዋል ። የቤተ ክርስቲያን አባት ነው ተብሎ ከሊቃውንት ተቆጥሮ ስለ ቅ. ማርያም ያልጻፈ አርሷንም ያላመሰገነ ከቶ የለም ። ግን በጐላ ካመሰገኑት ድርሰትም በሰፊው ከጻፉት ጥቂቶቹን እንዘረዝራለን ።

፩ኛ. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ነው ፥ እርሱም በድርሰቱ «እሰግድ ለኪ ወእዌድሰኪ . . . » እያለ አመስግኗታል ።
፪ኛ. ቅዱስ ደቅስዮስ ምስጋናዋን በመግለጥ ታዳጊነቷን ተአምሯን በመዘርዘር ጽፏል፤ እርሱም አመስግኗል ።
፫ኛ. ቅ ኤፍሬም ልዩ ልዩ ድርሰት በመጻፍ የቅ| ማርያምን ምስጋና ገልጧል ፤ እርሱም አመስግኗል ፤ ከዚያም በበለጠ የታወቀው የ፯ ቀን ውዳሴ ማርያም ነው ። ፬ኛ አባ ሕርያቆስ የነቢያትን ትንቢት አማናዊ በማድረግ ትርጕሙን በማስፋፋትና በመዘርዘር ፥ በቅዳሴ ድርሰቱ አመስግኗል ፤ እስካሁንም ድረስ በዚሁ ትመሰገናለች ። ሌሎችም ሊቃውንት እንዲሁ ጽፈዋል አመስግነዋል ። በኛ አገርም አባ ጊዮርጊስ አርጋኖነ ውዳሴን ጽፎ



ለምስጋና ስላቀረበ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያናት ሁሉ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ልዩ ልዩ ድርሰቶች ሰብስበው በአማን ውድስት ፤ በአማን ቅድስት በአማን ክብርት እያሉ ያመሰግኗታል ፤ እንድታማልዳቸው ይለምኗታል ።

## ምዕራፍ ፪።

## የእመቤታችን የሕይወት ታሪክ ።

ቅድስት ማርያም ከብዙ ትንቢት ከብዙ ብሥራት በኋላ ከደጋግ ቤተሰብ ከቅዱስ ኢያቄምና ከቅድስት ሐና በሕግ ተወለደች ። ቅድስት ማርያም የብፅዓት ልጅ ስለ ነበረች እንደተወለደች በእናቷ በአባቷ ቤት ብዙ ጊዜ አልተቀመጠችም ። ኢያቄምና ሐና ምንም ብዙ ዘመን መክነው ቆይተው ቢወልዱና የልጅም ፍቅር በጸና ቢኖርባቸው ፍቅሯን ፥ እስኪጠግቡ በቤት ሊያቆይዋት አልፈቀዱም ። እንዲሁ በተወለደች በ፫ኛው ዓመት ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው አስቀመጧት ለሊቀ ካህናቱ ለዘካርያስም ሰጡት እንጅ ፤ እርሱም በክብር ተቀብሎ የምግቧን ነገር ብቻ ሲያወጣና ሲያወርድ ከቤተ መቅደስ ተቀምጣ ምን ተበላለች ማንስ ያረጋጋታል እያለ በባሕረ ሐሳብ ሲዋኝ ፤ ሐሳቡን ሳይፈጽም እግዚአብሔር ለወዳጁና ለለመነው ሁሉ ቅርብ ስለሆነ በተለይም በብሥራተ መልአክ የተወለደችውን ቅድስት ማርያምን ያለ ጠባቂ መልአክ ያለመጋቢ መልአክ አልተዋትምና ፋኑኤል የተባለውን መልአክ ሰማያዊ ኅብስትን ሰማያዊ መጠጥን

www.ethiopianorthodox.org

አስይዞ ላከው ። መልአኩም ከእግዚአብሔር የተላከውን ምግብ አምጥቶ ስለመገበት የምግብዋ ነገር ከተያዘ ከሰው ጋር ምን ያጋፋታል በማለት መቀደስ አስገብቶ ዘግቶ ሔዷል ። ቅድስት ማርያም በብሥራተ መልአክ በብፅዓት የተወለደች ስለሆነች የእግዚአብሔር መልአክ ከቶ አልተለያትም ። እንዲያውም ፩ መልአክ ብቻ ሳይሆን ብዙ መላእክት እያረጋጓት መላእክት እየመገቧት በቤተ መቀደስ ፲፪ ዓመት ኖረች ።

፬/ በቤተ ዮሴፍ ፤ በቀደሙ በዕብራውያን ልምድ ሴት በ፲፭ ዓመቷ ለአቅመ ሔዋን እንደምትደርስ ስለሚገመት ለክፋት ጥበበኞች ለደግ ነገር ሰነፎች የሆኑ እመቤታችን ፲፭ ዓመት መሆንዋን በዘመን አቈጣጠር ተረዱና ቤተ መቅደሳችንን ታሳድፍብናለች በማለት ስለተጠራጠሩ ከቤተ መቅደሳችን ትውጣልን ብለው ሊቀ ካህናቱን ዘካርያስን ጠየቁ ፤ ዘካርያስም ስቀበላት በሕዝብ ፊት ነበር አሁንም በሕዝብ ፊት መውጣት አለባት ብሎ ስለመለሰላቸው የእሥራኤል ሽማግሎች ሁሉ ግማሹም በደግነት ግማሹም በክፋት ለመምከር ተሰበሰቡ ። ዘካርያስም ሽማግሎችን ካህናቱንም ሰብስቦ ከመከረ በኋላ ሚስቶቻችሁ የሞቱባችሁ በትር በትራችሁን አምጡልኝ ብሎ አዘዛቸው ። እነርሱም ግማሹ በክፋት ግማሹም በደግነት እየቸኰሉ ሳይውሉ ሳያድሩ እንደጠየቀው ወሰዱለት ። ከነዚያም ውስጥ ዮሴፍ የተባለ ሚስቱ የሞተችበት ደግ ሽማግሌ ሰው በትሩን አምጥቶ እንደሌሎቹ ሁሉ ሰጠ ።



ሊቀ ካህናቱ በ፲፪ ሰዓት ከምሽቱ አስገብቶ ሲጸልይበት አድሮ ቢያወጣው ከዮሴፍ በትር ላይ ዮሴፍ ሆይ እጮኛህ ማርያምን ጠብቃት የሚል ቀርፅ ተገኘ በት ፤ ርግብ ወዲያው አረፈችበት ፤ ዕጣም ቢያወጡ በርሱ ላይ ወጣበት ። ስለዚህ ይህን ምልክት እንደ ሦስት ምስክር አድርገው እርሱን ጠብቅ ብለው ሰጡት ። ዮሴፍም ከቤቱ አስገብቷት ወደ ንግዱ ሄደ ። (ነገረ ማርያምን ተመ)

፭ የጽንስ ነገር ፤ እመቤታችን ቅድስት ማርያም እንደሌሎች ድንግሎች ዋዛ ፈዛዛ ጨዋታ ቧልታ የማያታልላት ጊዜዋን በከንቱ የማታጠፋ ድንግል ነበረች ።

እንዲሁም ከሁሉ የከፋውና የኃጢአት መሠረት የሆነው ሥራ ፈትነት ከቶ አላገኛትም ፤ በቁም ነገር ጸንታ ቅዱሳት መጻሕፍትን በመመልከት በጐ አድራጐትን በመፈጸም ጊዜዋን ታሳልፍ ነበረች እንጅ ፤ በዚሁ መሠረት እንዳስለመደች በጐ አድራጐትን ለመሥራት ሰዎችን ለመርዳት ውኃ ለመቅዳት ወንዝ ወርዳ ሳለ ከእግዚአብሔር ፊት የሚቆም ቅዱስ መልአክ ስሙ ገብርኤል የተባለ (ሉቃ ፩፥ ፳፰) መጥቶ ‹ጸጋንና ክብርን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከንች ጋር ነውና ፤ እነሆ ትጸንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ ፣ እርሱም ሕዝቡን ከኃጢአታቸው የሚያነፃቸው ነው ፤ የልዑል እግዚአብሔርም ልጅ ይባላል ፤ ልዑል አምላክ የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ፤ በያዕቆብ ወገን ለዘለዓለም ነግሦ ይኖራል ፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ

www.ethiopianorthodox.org

በሉ መታሰቢያዋን ሰጥቶ ስሟን አስጠርቶ ዝክሯን አዝክሮ እነሆ እስከ ልጅ ልጅ አድርሶ ይገኛል ፤ በተለይም አገራችን ኢትዮጵያ ራሷ የቅድስት ማርያም የአደራ ስጦታ ሀገር ናት ብለን እናምናለን ፤ ስለዚህ በየዕለቱ ክርስቲያን ሁኖ « ሰአሊ ለነ ቅድስት » የማይላት የለም ፤ እመቤታችንም ቃል ኪዳኗን በመጠበቅ አማላጅነቷን በመፈጸም ከልጅዋ ከወዳጅዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ እየለመነች ፍቅር አንድነት እንዲበዛ ሰላም እንዲነግሥ ባዕድ እንዲርቅ ስትረዳን ኑራለች እንዲሁም ትኖራለች ። የቅድስት ማርያምን አማላጅነት እስከ ፲፯ኛው መቶ ዓመት ድረስ በመላ ቤተ ክርስቲያን ትቀበለው ነበረች ፤ ግን በዚህን ጊዜ ከተነሣው ንቅናቄ ጥቂቶች ሲቃወሙ አሁንም ቢሆን ጥንታውያን ወይም የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በሚባሉት ዘንድ እስካሁን እንደተጠበቀ ይገኛል ።

## ማ ጠ ቃ ለ ያ ፤

ቅድስት ማርያም በነቢያት ትንቢት ተጸንሳ የተወለደች በመንፈሳዊ አመራር ያደገች መንፈስ ብርቱ ድንግል ናት ። ድንግል ማርያም ከተወለደችበት ዕለት ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ያልተለያት የልጃገረዶች ሥጋዊ ስሜት ያላደረበት ጉልማሶች በሽቱ ያላታለሏት ያላገባች እጮኛ፣ የወለደች ድንግል ናት ። ቅድስት ማርያም ተስፋ ለቆረጡት የታመነች ተስፋቸው የኃጥአን አማላጅ የጻድቃን ሞገስ የመላእክት እህት የሰው ሁሉ አማላጅ ናት ።



የጠፋው ልጅነት የተገኘበት ያረጀው ልጅነት የታደሰበት በርሷ አማካይነት ነውና ። የቅድስት ማርያም ጌጥ ሥጋዊ አልነበረም ፤ የርሷ ጌጥ ንጽሕናዋ ቅድስናዋ ነበር ። ስለዚህ ቅድስተ ቅዱሳን ትባላለች ። ይኸ ሁሉ ሲሆን ቅድስት ማርያም የትሑቶች ምሳሌ ራሷን ዝቅ የምታደርግ እመቤት ነበረች ፤ መጽሐፈ ኢሳይያስ ስታነብ በድንግልና ጸንሳ በድንግልና ወንድ ልጅ የምትወልድ አለች ብሎ ነቢዩ ኢሳይያስ ከተናገረው ምዕራፍ ስትደርስ ለዚያች ድንግል እኔ አሽከር ሁኜ አገለግያት ፤ በረከቷን ተሳትፌ ብላ ተመኘች እንጅ ወይ እኔ በሆንኩ ፤ የሚል ምኞት አላደረባትም። የትሕትናዋ ተመልካች ልዑል አምላክ ግን ለርሱ ማኅደር ትሆን ዘንድ እርሷን መረጠ ፤ ከርሷም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆነ ።

ቅድስት ማርያም ለሰው ልጅ ድኅነት አሳቢ የሰው የድካሙ የችግሩ ተካፋይ ናት ፤ ለምሳሌ ከሠርግ ቤት ሄዳ የባለሠርጎች ወይን ቢያልቅባቸው ከነርሱ የበለጠ እርሷ ተቸግራ ልጅዋን ወዳጅዋን እንዲያበረክተው ለመነችው ፤ የምልጃዋንም ሥራ ቀጠለች ፤ እንዲህ ስትል ‹ ወይኑ አልቆባቸዋል › ። የናት ልመና ፊት አያስመልስ አንገት አያስቀልስ እንደተባለው መልሳ መላልሳ ከመለመኗ የተነሣ ክርስቶስ የመጀመሪያውን ተአምራት በርሷ አማካይነት በሠርግ ቤት ገለጠ ፤ ማለት የጠራውን ምንም ያልተቀላቀለበትን ውኃ ፍጹም ወይን አደረገ (ዮሐ ፪፥ ፩-፲፪) ።

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ሁሉ ምክንያት በክርስቲያኑ ዓለም ሁሉ ቅድስት ማር
ያም የኀዘንተኞች አጽናኝ ፤ የክርስቲያኖች ደጋፊ ፣ የደሆች
መጠጊያ የችግረኞች ወደብ፤የዕውራን መርሕ የደከሞች ምር
ኩዝ፤ የስደተኞች አረጋጊ አገር አስለማጅ የደሀ ስንቅ የደሀ
አደጎች ሞግዚት የደናግል መመኪያ እንደሆነች ይታ
መንባታል ። ሊቃውንትም እንዲሁ እያሉ አመስግነዋታል።
በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን
በላይ ሁና ቅድስት ማርያም ስትመሰገን ትኖራለች ፣ ፈጣሪ
ናት ሳንል የፈጣሪንም ምስጋና ለርሷ ሳንሰጥ ወይም እርሷ
አምላክ ናት ሳንል የአምላክ እናት ስለሆነች አምላክን
ስለወለደች እርሱ ስላከበራት እናከብራታለን ፣ ለርሷ የሚ
ገባውን ክብር እንሰጣታለን ።

ለርሷ የሚገባውን ምስጋና እናቀርብላታለን ፤ አማላ
ጅነቷን እናምናለን እንዲሁም እናሳምናለን ። አምላክ
የምሕረት የአማላጅነት ቃል ኪዳን ስለሰጣት ቃል ኪዳ
ኗን እናምናለን ስሟን እንጠራለን መታሰቢያዋን እናደ
ርጋለን ቤተ መቅደሷን እናንጻለን ድርሳኗን ውዳሴዋን
እንጽፋለን ፤ በዚህም ሁሉ ምክንያት የእመቤታችን በረከ
ትና አማላጅነት ከኛ ከቶ ተለይቶ አያውቅም ። አሁንም
የቅድስት ማርያም አማላጅነት የልጅዋ ምሕረት በሁላችን
ላይ ለዘለዓለም ይሁን ።

በሰላም አስጀምሮ በሰላም ላስፈጸመን አምላክ ዘለዓለማዊ
ምስጋና ይገባው አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org